# ሰሞነኛ (4)

## ጋን በጠጠር ይደገፋል

## በሎስ አንጀለስ የኢትዮጵያ ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት

**ታህሳስ/2001**

**December /2008**




**Consulate General of Ethiopia**

**3460 Wilshire Blvd #308**

**Los Angeles, CA 90010**

**Tel: 213 365 6651 Fax: 213 365 6670**

www.ethioconsulate-la.org

# ጋን በጠጠር ይደገፋል

ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከመካከለኛው ምስራቅ እስከ ሩቅ ምሥራቅ ፣ከአሜሪካ እስከ አውስትራሊያ ተሰራጭተው የዕለት ጉሮሮቸውን ለመድፈን ሲሯሯጡ ይስተዋላል፡፡ በያሉበት ኑሮ ውስጥ የሚወዷትን አገር ሳያስቡ የዋሉበት ጊዜ የለም፡፡ «አንድን ሰው ከገጠር ማውጣት ይቻል ይሆናል ገጠሩን ግን ከሰውየው አዕምሮ ማውጣት ይቻልም» የሚለው አባባል ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው ፣ለህዝባቸውና ለቤተሰቦቻቸው ያላቸው በጎ አስተያየትና ፍቅር አጉልቶ የሚያሳይ ነው ቢባል ከዕውነት የራቀ አይደለም፡፡

በውጭ የሚገኝ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊ የተሰማራበት የሙያና የተግባር መስክ የተለያየ ቢሆንም ከአገሩ ጋር የሚያገናኘው ክር እንዳይላላ ራሱን በማህበራዊ ተቋማት ውስጥ በማሰባሰብ ኢትዮጵያዊነቱን ለማሳየት ይጥራል፡፡ በኮሚኒቲ፣በልማት፣በዕምነት ፣በዕድር፣ዕቁብ፣በትምህርት በሞያ ፣በአብሮ አደግ ፣ወ.ዘ.ተ ስብስቦችን በማደረጀት ስለ አገሩ ይወያያል፣ይመክራል፣ይዘክራል፡፡

በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊና ትውልድ ኢትዮጵያዊ በባዕድ አገር በመሰባሰብ ብቻ ሳይወሰን በአገሩ የሚገኙ ቤተሰቦቹንና ዘመድ አዝማዶቹን ለመርዳት ገንዘብ በመላክ ጎጂቸውን ይደግፋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከውጭ ቤተሰብን ለማገዝ መቻሉ ከዘመድ አዝማድ ኑሮ መታደግ ባሻገር ለአገር እድገትና ልማት አስፈላጊ የሆነውን የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ደረጃ ትልቅ አስተፅኦ እንዳለው የተረጋገጠ ነው፡፡በአንድ በኩል ቤተሰብን ደግፎ በሌላ በኩል ደግሞ ለአገራችን ልማት የሚያግዝ የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት ልማታችን በማገዝና በመደገፍ በኩል የማይናቅ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡

በውጭ የሚገኝ ኢትዮጵያዊና ትውልድ ኢትዮጵያዊ በሚያበረታታ መልክ በስፋት የሚሳተፍበትና እያደገ የመጣው ሌላው ተሳትፎ ንግድና ኢንቨስትመንት ነው፡፡
በአገራችን የሚካሄድ ልማት ሰፊና የተለያየ በመሆኑ በውጭ አገር የሚገኙ ወገኖቻችን ባላቸው የገንዘብና የሞያ ብቃት መሰረት በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ በግብርናው ዘርፍ በሰሊጥ፣ በጥጥ፣ ጃትሮፓ፣በከብት ማደለብ፣በወተት ሀብት ልማት ዘርፍ በመሳትፍ ምርት ማምረት የጀመሩ የዲያስፖራ አባላት በርካታ ናቸው፡፡ ከግብርናው ዘርፍ ሌላ በትራንስፖርት ፣ በሆስፒታልና በከፍተኛ የጤና ተቋማት ፣በትምህርት ተቋማትና በማስልጠኛ ግንባታ፣በሆቴል፣በአስጎብኚና የጉዞ ወኪል የሚሳተፉ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን እያደገ መጥቷል፡፡በተመሳሳይ በኤክስፖርትና

ኢምፖርት ፣በጅምላና በችርቻሮ ንግድ ስራዎች በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከመሀል አዲስ አበባ እስከ ትንንሽ ወረዳዎች ድረስ በአካል በመገኘት ሆነ በህጋዊ ወኪሎች አማካኝነት ይሳተፋሉ:: በአጠቃላይ በኢንቨስትመንትም ሆነ በንግድ የሚሳተፉ የዲያስፖራ አባላት አገራችን ሰርተው ሊያድጉባት የሚችሉባት መሆኗን በልበ ሙሉነት ይመሰክራሉ::

በኢንቨስትመንት የሚሳተፉ በውጭ የሚገኙ ወገኖቻችን በየሚኖሩባቸው አገሮች ከሚገኙ ኢምባሲዎች ወይም ቆንስላ ጽ/ቤቶች ጋር በመመካከርና በመደጋገፍ የጀመሯቸው የኢንቨስትመንት ተግባሮች በአመዛኙ ውጤታማ ሲሆኑ ይህም የምክክር አካሄድ በአገር ቤት በውጭ ጉዳይ የኮሚኒቲ ጉዳዮች ዋና ዳሬክቶሬት እንዲሁም በክልሎች በተመሰረቱ የዲያስፖራ አስተባባሪዎች ጋር እንዲተሳሰሩና አስፈላጊ የስራ መደጋፎች እንዲኖሯቸው መንገዶችን ከፍቷል::

በሌላ በኩል በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው የውጭ ምንዛሬ ሂሳብ እንዲከፍቱ መፍቀድ የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንትን የሚበረታታ መሆኑን መንግስት በመረዳቱና እነዚሁ አካላት የውጭ ምንዛሬ እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ የአገሪቱን የአለም አቀፍ መጠባበቂያ ሂሳብ የሚደግፍ ስለሚሆንና ለቀጥተኛ የአገራችን ኢንቨስትመንት ፍሰት አስተዋፅኦ ያደረጋል ተብሎ ስለሚታሰብ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ታህሳስ 22 ቀን 1996 (ዲሴምበር 31/2004) በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በአገር ውስጥ ባንኮች የውጭ ምንዛሬ ሂሳብ የሚከፍቱበት መመሪያ ወጥቶ ተግባራዊ ሆኗል::

በዚህ መመሪያ መሰረት ሂሳቡን ለመክፈት መብት የተሰጣቸው በውጭ የሚኖሩ ግለሰቦች በአካል በመቅረብ ወይም በፖስታ ሂሳብ መክፈት ይችላሉ::ነገር ግን ሂሳብ ከፋቹ የማመልከቻ ደብዳቤና የፊርማ ማረጋገጫ ሰነድ አያይዞ ማቅረብ ግዴታ አለበት::በዚህም መሰረት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የጊዜ ገደብ ተቀማጭ፣ተንቀሳቃሽ ሂሳብ እንዲሁም ወደ ውጭ ሊወጣ የሚችል የብር ሂሳብ (Non-reparable birr account) ይህም በቁጠባ ሂሳብ መልክ ሆኖ በአገር ውስጥ ለሚደረጉ ወጪዎች ብቻ የሚውል አይነት ሂሳቦች መክፍት ችላሉ:: ህጋዊ ወኪሎች በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በመወከል የውጭ ምንዛሬ ሂሳብ እንዲከፍቱ እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ ወደ ሂሳቦቹ እንዲያስገቡ አይፈቀደም:: ነገር ግን ወኪሉ ከውጭ ምንዛሬ ሂሳብ ወጪ እያደረገ በአገር ውስጥ በብር ለሚፈፀሙ፣ወደ ሌሎች የውጭ ምንዛሬ ሂሳቦች ለማስተላለፍ፣ለገቢ ንግድና ለሌሎች

የውጭ አገልግሎት ክፍያዎች፣ወደ ውጭ አገር ለማስተላለፍ፣በገበያ ላይ ባለው የምንዛሬ ምጣኔ መሰረት ወደ ብር ሂሳብ ለመለወጥ ፣የባንክ አገልግሎት ክፍያን ለመፈፀም፣ለብድር ወይም ለጨረታ እንደ ዋስትና ወይም መያዣ ለማገልገል፣የተንቀሳቃሽ ሂሳብ ቼክ በመፃፍ እና የገንዘብ ማውጫ ፎርም በመሙላት ወይንም በሌላ በቅድሚያ የተዘጋጀ ሥርአት ወጪ ለማድረግ የውጭ ምንዛሬ ሂሳብ ባለቤት በህጋዊ መንገድ በግልፅ የወከለው ከሆነ ከዚሁ ሂሳብ በአገር ውስጥ ገንዘብ ወጪ ለማድረግ በመመሪያው የተፈቀደ ሲሆን፣ የተንቀሳቃሽ የውጭ ምንዛሬ ሂሳብ ለመክፈት አነስተኛው የመነሻ ተቀማጭ 100 ዶላር ሆኖ የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሂሳብ ለመክፈት አነስተኛው መነሻ ተቀማጭ 500 ዶላር ወይም ከዚሁ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የተፈቀዱ የውጭ ምንዛሬ ገንዘቦች መሆኑ ተጠቅሷል።የውጭ ምንዛሬ ለመክፈት የተፈቀዱ ገንዘቦች የአሜሪካን ዶላር፣የእንግሊዝ ፓውንድ እና ዩሮ ናቸው።

ይህ የብሄራዊ ባንክ መመሪያ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በአገር ቤት የሚካሂዱት የንግድና የኢንቨስትመንት ተግባራት በተቀላጠፈ መልክ እንዲያከናወኑ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ሲባል የተወሰደ ርምጃ ነው።

ይህ መመሪያ ከወጣ የተወሰኑ ዓመታት ቢሆንም በሚፈለገው መልክ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትጵያውያን ሲጠቀሙበት አይታይም። ከሁሉም በላይ መመሪያው ስለመኖሩ የሚያውቀው ሰው በጣም አናሳ ነው።መመሪያው መውጣቱ የሚታወቅ ቢሆንም እንኳ በመመሪያው ውስጥ የሰፈሩ መሰረታዊ ሀሳቦችን የተረዳው ሰው በጣም ጥቂት ነው።ያም ሆኖ ግን በአገር ውስጥ በሚገኙ ባንኮች ብሄራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ መሠረት የውጭ ምንዛሬ ሂሳብ የሚከፍቱ ኢትጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የጀመሯቸው የልማት ተግባራት ስሉጥ እንደሆነላቸው ይገልፃሉ።

አገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት ተቆራኝቷት ከቆየ ድህነት ለመውጣት ዕድገትን ፈጣን በሆነ ልማት አማካኝነት ማስመዝገብ እንደሚኖርባት የኢትዮጵያ መንግስት ያምናል።ይህን ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማምጣት ደግሞ ንግድና ኢንቨስትመንት ማስፋፋትና ምቹ ሁኔታ መፍጠር ከቶውን ችላ የሚሉት ተግባር አይደለም። በውጭ የሚገኙ ወገኖቻችን በስደት ኑሯቸው ያገኙትን ገንዘብና ዕውቀት በአገራችን ለሚካሄደው ልማት ሊያውሉት የሚገባበት ወቅት አሁን ነው። ዘወትር አገራችን ደሀ ናት ከማለትና ርሀብና ችግር በተነሳ ቁጥር ከመሸማቀቅ ለመውጣት የሚቻለው በተደጋገፈ ተሳትፎችን በአገራችን የሚካሄደውን ልማት ስንደግፍ በመሆኑ፣ በተለይ በኢንቨስትመንት፣በንግድ

በመሰማራትና በአገር ቤት የሚገኙ ወገኖቻችን በገንዘብ በመደገፍ በኢትዮጵያ የሚካሄደውን የልማት እንቅስቃሴ አጠናክረን እንድንቀጥል የተለመደ ጥሪያችንን እናቀርባለን።